

# በጣራው በኩል

- ኢየሱስ ክርስቶስ በቅፍርናሆም ከተማ በአንድ ቤት ውስጥ ነበር። እርሱ በነበረበት ቤት ውስጥም እጅግ ብዙ ሰዎች ተጨናንቀው ቆመው ስለነበር ማንም አልፎ ወደደኢየሱስ መቅረብ የሚችል ሰው አልነበረም።

- የተወሰኑ ሰዎችም የታመመ ጓደኛቸውን ወደኢየሱስ ይዘውት መጡ። ሰውዬው በፍፁም መንቀሳቀስ የማይችል ሽባ ነበር። ጓደኞቹ ኢየሱስ እንደሚፈውሰው አምነው ነበርና ኢየሱስ ወዳለበት ቤት ይዘው መጡ። ሆኖም ከሕዝቡ ብዛት የተነሳ ኢየሱስ ያለበት ቦታ መድረስ አልቻሉም።

- ስለዚህ አንድ ሀሳብ መጣላቸው። ወደቤቱ ውስጥ መግባት የሚችሉበት ሌላ መንገድ መፈለግ! ይህም መንገድ ጣራው ላይ መውጣትና ከጣራው የተወሰነውን ነቅሎ ቀዳዳ ማበጀት ነበር ሀሳባቸው። ይህንንም ሳይዘገዩ አደረጉት። ከዚያም ወዳጃቸው ተኝቶበት የነበረበትን አልጋ በገመድ አስረው ኢየሱስ በቤቱ ውስጥ ባለበት አቅጣጫ ወደታች አወረዱት።

- ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሰውዬውን፣ “ልጄ፣ ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል፣” አለው።

- አንዳንድ በዚያ የነበሩ የአይሁድ መሪዎች እንዲህ ብለው አሰቡ፣ “ኃጢአትን የማሰተሰረይ ስልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ታዲያ እንዴት ነው ይህ ሰው ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል ለማለት የደፈረው?” ብለው በልባቸው አሰቡ።

- ኢየሱስም ሃሳባቸውን አውቆ ፣ “ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል ከማለትና  አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማለት የትኛው ይቀላል?” ብሎ ጠየቃቸው። በእርግጥም የሚቀለው፣ “ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል፣”ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን ይህንን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምንም መንገድ አልነበረም።

- ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን ይቅር የማለት ስልጣን እንዳለው ለማሳየት ከበድ ያለውን ነገር አደረገ። ሰውዬውን፣ “ተነሳና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ፣” አለው። ይህ በፍፁም መንቀሳቀስ የማይችለው ሰው ተነስቶ መራመድ ጀመረ። ኢየሱስ ከተናገረው ቃል የተነሳ የሆነውን ነገር ሁሉም ሰው በአይኑ አየ።

- ሰዎች አይናቸውን ማመን አቃታቸው። እንዲህ አይነት ኃይል አይተው አያውቁምና!

*የዚህን በጣራ በኩል ወደታች ወርዶ ፈውስ ያገኘ ሰው ታሪክ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 2፡ 1 – 12 ውስጥ ማንበብ እንችላለን።*

http://gardenofpraise.com